Vaccinate WA

# ደካማ በሽታ የመከላከል አቅም ላላቸው ሁሉም ሰዎች የ COVID-19 ክትባት ማጣቀሻ መምሪያ

ደካማ በሽታ የመከላከል አቅም ያላቸው ሰዎች COVID-19 ንጨምሮ በተለይም ለኢንፌክሽኖች ተጋላጭ ናቸው። **ከሚከተሉት የህክምና ሁኔታዎች ውስጥ አንዳቸውም ካለብዎት በመጠኑ እስከ ከባድ የበሽታ መቋቋም አቅምዎ ያነሰ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ተጨማሪ የ COVID-19 ክትባት ተጨማሪ መጠን ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦**

- ለዕጢዎች ወይም ለካንሰሮች ንቁ የካንሰር ህክምና እያደረጉ ከሆነ
- የአካል ብልት ንቅለ ተከላ አድርገው የበሽታ መከላከያ ስርዓቱን ለማዳከም መድሀኒት እየወሰዱ ከሆነ
- ባለፉት 2 አመታት ውስጥ የስቴም ህዋስ ንቅለ ተከላ አግኝተው ወይም በሽታ የመከላከል ስርዓትዎን ለማዳከም መድሀኒት ከወሰዱ
- መካከለኛ ወይም ከባድ የመጀመሪያ ደረጃ የበሽታ መከላከያ እጥረት ካለብዎት (እንደ DiGeorge syndrome፣ Wiskott-Aldrich syndrome)
- የተራቀቀ ወይም ያልታከመ የ HIV ኢንፌክሽን ካለብዎት
- ከፍተኛ መጠን ባለው ኮርቲሲቶይዶይድ ወይም ንቁ ህክምና እየወሰዱ ከሆነ ወይም የበሽታ መከላከያ ምላሹን የሚገቱ ሌሎች መድሀኒቶች እየወሰዱ ከሆነ።

ይህ ዝርዝር ሁሉንም በሽታን የመከላከል አቅም የሚያዳክሙ ሁኔታዎችን አያካትትም፣ ተጨማሪ ዶዞች ለእርስዎ ጠቃሚ ይሆን እንደሆነ ለመወሰን እባክዎ የህክምና አቅራቢዎን ያነጋግሩ። ደካማ በሽታ የመከላከል አቅም ካልዎት፣ ከ COVID-19 ተጠብቀው ለመቆየት ምን ያክል ዶዞች ለመውሰድ ብቁ እንደሆኑ ለመመልከት ከታች ያለውን ካርታ ይመልከቱ፦

| ይህ ካለብዎት... | የዕድሜ ክልል | የመጀመሪያ ዙር | ተጨማሪ የሞኖቫለንት ዶዝ መውሰድ ያስፈልገኛል? | ማጠናከርያ ማግኘት እችላለሁ? |
|---|---|---|---|---|
| **Moderna** | ከ 6 ወር እስከ 4 ዓመት ዕድሜ | ሁለት ዶዞች በ 28 ቀናት ልዩነት ይሰጣሉ | አዎ፣ ከሁለተኛው ዶዝዎ ከ 28 ቀናት በኋላ ተጨማሪ ዶዝ መውሰድ አለብዎት። | አዎ፣ ከ 6 ወር እስከ 4 ዓመት የሆኑ ልጆች መውሰድ ያለባቸው እንደ የመጀመሪያ ተከታታያቸው አንድ ዓይነት ብራንድ ያለውን የዘመነ ባይቫለንት ዶዝ ነው። |
| | 5 ዓመት ዕድሜ | ሁለት ዶዞች በ 28 ቀናት ልዩነት ይሰጣሉ | አዎ፣ ከሁለተኛው ዶዝዎ ከ 28 ቀናት በኋላ ተጨማሪ ዶዝ መውሰድ አለብዎት። | አዎ፣ 5 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች የ Pfizer ወይም Moderna የዘመነ ባይቫለንት ማጠናከሪያ ዶዝ መውሰድ አለባቸው። |
| | 6+ ዓመት ዕድሜ | ሁለት ዶዞች በ 28 ቀናት ልዩነት ይሰጣሉ | አዎ፣ ከሁለተኛው ዶዝዎ ከ 28 ቀናት በኋላ ተጨማሪ ዶዝ መውሰድ አለብዎት። | አዎ፣ 6 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሰዎች ወቅታዊ እንዲሆኑ የዘመነ ባይቫለንት የ Pfizer ወይም Moderna mRNA ማጠናከሪያ ከመጨረሻው ዶዝ ከ 2 ወራት በኋላ ይመከራል።<br>ከዚህ ቀደም ማጠናከሪያ ያልወሰዱ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሰዎች የዘመነ የ mRNA ማጠናከሪያ የማይወስዱ ወይም መውሰድ የማይችሉ ከሆነ የመጀመሪያ ዙራቸውን ካጠናቀቁ ከ 6 ወራት በኋላ የ Novavax ማጠናከሪያን ለመውሰድ ሊመርጡ ይችላሉ። |
| **Pfizer** | ከ 6 ወር እስከ 4 ዓመት ዕድሜ | **ሶስት ዶዞች፦** የመጀመሪያዎቹ ሁለት ዶዞች በ 21 ቀናት ልዩነት ይሰጣሉ፤ ከ 8 ሳምንታት በኋላ ሶስተኛ ዶዝ። | በዚህ ጊዜ ምንም ተጨማሪ የመጀመሪያ ዶዝ የለም። | አይ፣ ከ 6 ወር እስከ 4 ዓመት ላሉ በዚህ ጊዜ የ Pfizer የመጀመሪያ ተከታታይን ከወዲሁ ላጠናቀቁ የዘመነ የባይቫለንት ዶዝ ፈቃድ የለውም። |
| | 5 ዓመት ዕድሜ | ሁለት ዶዞች በ 21 ቀናት ልዩነት ይሰጣሉ | አዎ፣ ከሁለተኛው ዶዝዎ ከ 28 ቀናት በኋላ ተጨማሪ ዶዝ መውሰድ አለብዎት። | አዎ፣ Pfizer የወሰዱ 5 ዓመት የሆናቸው ልጆች መውሰድ የሚችሉት የዘመነ Pfizer ባይቫለንት ማጠናከሪያን ብቻ ነው። |
| | 6+ ዓመት ዕድሜ | ሁለት ዶዞች በ 21 ቀናት ልዩነት ይሰጣሉ | አዎ፣ ከሁለተኛው ዶዝዎ ከ 28 ቀናት በኋላ ተጨማሪ ዶዝ መውሰድ አለብዎት። | አዎ፣ 6 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ወቅታዊ እንዲሆኑ ከመጨረሻው ዶዝ 2 ወራት በኋላ የዘመነ ባይቫለንት የ Pfizer ወይም Moderna mRNA የማጠናከሪያ ዶዝ ይመከራል።<br>ከዚህ ቀደም ማጠናከሪያ ያልወሰዱ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሰዎች የዘመነ የ mRNA ማጠናከሪያ የማይወስዱ ወይም መውሰድ የማይችሉ ከሆነ የመጀመሪያ ዙራቸውን ካጠናቀቁ ከ 6 ወራት በኋላ የ Novavax ማጠናከሪያን ለመውሰድ ሊመርጡ ይችላሉ። |
| **Johnson & Johnson** | 18+ ዓመት ዕድሜ | አንድ ዶዝ | አዎ፣ ከ 1ኛው የ J&J ዶዝ ከ 28 ቀናት በኋላ ከ mRNA ክትባት ጋር ተጨማሪ ዶዝ መውሰድ አለብዎት። | አዎ፣ ወቅታዊ እንዲሆኑ የዘመነ ባይቫለንት የ Pfizer ወይም Moderna mRNA ማጠናከሪያ ከመጨረሻው ዶዝ ከ 2 ወራት በኋላ ይመከራል።<br>ከዚህ ቀደም ማጠናከሪያ ያልወሰዱ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሰዎች የዘመነ የ mRNA ማጠናከሪያ የማይወስዱ ወይም መውሰድ የማይችሉ ከሆነ የመጀመሪያ ዙራቸውን ካጠናቀቁ ከ 6 ወራት በኋላ የ Novavax ማጠናከሪያን ለመውሰድ ሊመርጡ ይችላሉ። |
| **Novavax** | 12+ ዓመት ዕድሜ | ሁለት ዶዞች፣ በ 21 ቀናት ልዩነት ይሰጣሉ | በዚህ ጊዜ ምንም ተጨማሪ የመጀመሪያ ዶዝ የለም።. | አዎ፣ 12 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሰዎች ወቅታዊ እንዲሆኑ የዘመነ ባይቫለንት የ Pfizer ወይም Moderna mRNA ማጠናከሪያ ከመጨረሻው ዶዝ ከ 2 ወራት በኋላ ይመከራል።<br>ከዚህ ቀደም ማጠናከሪያ ያልወሰዱ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆናቸው ሰዎች የዘመነ የ mRNA ማጠናከሪያ የማይወስዱ ወይም መውሰድ የማይችሉ ከሆነ የመጀመሪያ ዙራቸውን ካጠናቀቁ ከ 6 ወራት በኋላ የ Novavax ማጠናከሪያን ለመውሰድ ሊመርጡ ይችላሉ። |

# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### በተጨማሪ የክትባት ዶዝ እና በማጠናከርያ የክትባት ዶዝ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ተጨማሪ ዶዝ የመጀመሪያውን ክትባት ተከታታይን ላጠናቀቁ (ከላይ ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ) ነገር ግን በቂ ጠንካራ የበሽታ መካለከል ምላሽ ሌላቸው ታካሚዎች የሚሰጥ ነው።

የማጠናከሪያ ዶዝ የመጀመሪያው የክትባት ዙር በጊዜ ሂደት ከቀነሰ በኋላ በሽታ መከላከልን ወይም የመከላከል አቅምን ለማጎልበት ወይም ለመመለስ ለታካሚዎች የሚሰጥ ነው።

### ከ COVID-19 ለሚመጣ ከባድ ህመም ከፍተኛ የመያዝ ዕድል እንዲኖርዎ ስር የሰደዱ የህክምና ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?

ከታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ያሏቸው በማንኛውም ዕድሜ ላይ ያሉ ሰዎች (በእንግሊዘኛ ብቻ) በ COVID-19 በጠና የመታመም ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።

በተለይ በዕድሜ ከገፉ ወይም በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያሉትን ጨምሮ ብዙ ወይም ከባድ የጤና እክሎች ካሉብዎት፣ የ COVID-19 ክትባቶች (የመጀመሪያ ዶዝ እና ማጠናከርያዎች) እና ሌሎች ለ COVID-19 የመከላከያ እርምጃዎች አስፈላጊ ናቸው። ይህ ዝርዝር እርስዎን በ COVID-19 ለከፋ ህመም ሊያጋልጡ የሚችሉ ሁሉንም ሁኔታዎች አያካትትም። እዚህ ያልተካተቱ ሁኔታዎች ካጋጠመዎት፣ ሁኔታዎን እንዴት በተሻለ ሁኔታ ማስተዳደር እንደሚችሉ እና እራስዎን ከ COVID-19 ለመከላከል የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።

- ካንሰር
- ሥር የሰደደ የኩላሊት በሽታ
- ሥር የሰደደ የጉበት በሽታዎች
- ሥር የሰደደ የሳምባ በሽታዎች
- የመርሳት በሽታ ወይም ሌሎች የነርቭ ሁኔታዎች
- የስኳር በሽታ (አይነት 1 ወይም 2)
- ዳውን ሲንድሮም
- የልብ ሕመም ሁኔታዎች
- የኤች አይ ቪ ኢንፌክሽን
- የበሽታ መቋቋም አቅም ማነስ ሁኔታ (የተዳከመ የበሽታ መቋቋም ስርዓት)
- የአእምሮ ጤንነት ሁኔታዎች
- ከመጠን በላይ ክብደት እና ከመጠን በላይ ውፍረት
- እርግዝና
- የሲክል ሴል በሽታ ወይም ታላሴሚያ
- ማጨስ፣ የአሁን ወይም የቀድሞ
- ጠንካራ የአካል ክፍል ወይም የደም ግንድ ህዋስ ንቅለ-ተከላ
- ወደ አንጎል የደም ፍሰትን የሚጎዳ የስትሮክ ወይም ሴሬብሮቫስኩላር በሽታ
- የዕፅ አጠቃቀም ህመሞች
- የሳንባ ነቀርሳ

### የዘመነ/ባይቫለንት ማጠናከሪያ ምንድን ነው?

የዘመነ/ባይቫለንት የ COVID-19 ማጠናከሪያ ከመጀመሪያው የኮሮና ቫይረስ ዝርያ የሚጠብቅ የበሽታ መከላከል አቅምን የሚጨምር እንዲሁም በአሁኑ ሰዓት ያሉ ህምሞች ላይ በብዛት ከሚታዩት አዳዲስ ዝርያዎች የሚጠብቅ የክትባት ቀመር ነው። የዘመኑ ማጠናከሪያዎች ከቫይረሱ በጣም ጥሩ ጥበቃ ለመስጠት እንዲሁም በጊዜ ሂደት የሚቀዥቀውን የክትባት ውጤታማነት ችግር ለመፍታት የታሰቡ ናቸው።

### መጠነኛ ወይም ከባድ በሽታን የመቋቋም አቅም ችግር ያለባቸው ሰዎች እነዚህን መጠኖች ለመቀበል የዶክተር ማስታወሻ/ማዘዣ ወይም ሌላ ሰነድ ያስፈልጋቸዋል?

አይ፣ ግለሰቦች እራሳቸውን ለይተው ማወቅ እና ክትባቶች በሚሰጡበት በማንኛውም ቦታ ሁሉንም መጠኖች መቀበል ይችላሉ። ይህ ለዚህ ህዝብ ተደራሽነት ተጨማሪ እንቅፋቶች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል። በሽታን የመቋቋም አቅም ችግር ያላቸው ግለሰቦች ስለ ልዩ የጤና ሁኔታቸው ጥያቄዎች ካላቸው፣ ተጨማሪ መጠን መውሰድ ለእነሱ ተስማሚ ስለመሆኑ ከጤና እንክብካቤ ሰጪያቸው ጋር መወያየት ይችላሉ።

### የ COVID-19 ክትባት ከተከተብኩ፣ አሁንም ሌላ ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይኖርብኛል?

አዎ፣ ቢከተቡም እንኳን፣ በተወሰኑ የህዝብ የቤት ውስጥ መሰብሰቢያ ስፍራዎች ውስጥ ማስክ እንዲያደርጉ ሊጠበቅብዎት ይችላል። በ ማስኮች እና የፊት መሸፈኛ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ገጽ (በእንግሊዘኛ) ላይ ተጨማሪ መረጃ ያግኙ። እጅዎን በተደጋጋሚ እንዲታጠቡ፣ የስድስት ጫማ ርቀትዎን እንዲጠብቁ እንዲሁም መሰባሰቦችን እንዲቀንሱ እንመክርዎታለን።

የ COVID -19 ክትባቶች በደንብ ይሠራሉ፤ ግን 100% ውጤታማ አይደሉም። አንዳንድ ሰዎች ክትባት ቢወስዱም እንኳ COVID-19 ሊያዙ ይችላሉ። ተላላፊነታቸው የጨመረ ተለዋጮች እየጨመሩ ባሉበት ወቅት፣ ሁሉም ሰዎች የቫይረሱን ስርጭትን ለመቀነስ እንደ ጭምብል መልበስ የመሳሰሉ ጥንቃቄዎችን ማድረግ አስፈላጊ ነው።

**ተጨማሪ ጥያቄዎች? ይጎብኙን፦ doh.wa.gov/covidbooster**

Washington State Department of Health

DOH 825-064 December 2022 Amharic

ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ በ 1-800-525-0127 ላይ ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም በ civil.rights@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።